# አቶ በረከት ስሞን ለፍርድ መቅረብ እንዳለባቸው የአውሮፓ ህብረት ፓርላማ አባል ወ/ሮ አና ጎሜዝ ገለጹ

October 21, 2017

አባይ ሚዲያ ዜና
ዘርይሁን ሹመቴ

የአቶ በረከት ስሞኦንን ከስልጣን መልቀቅ ተከትሎ የአውሮፓ ህብረት አባል የሆኑት ወ/ሮ አና ጎሜዝ አስተያየታቸውን ለአንባቢያን አስፍረዋል።
የአውሮፓ ህብረት አባል የሆኑትና በኢትዮጵያ መንግስት የሚፈጸመውን የሙብት ጥሰት በተደጋጋሚ በማጋለጥ የሚገኙት ወ/ሮ አና ጎሜዝ አቶ በረከት ስሞኦን ለፍርድ መቅረብ አለባቸው በማለት አስተያየት ሰጥተዋል።

የጠቅላይ ሚንስትር ሃይለማርያም የከፍተኛ ፕሮቶኮል ሃላፊ አገዛዙን በመክዳት በዩናይትድ ስቴትስ የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቃቸው በተሰማ ሰሞን የህዝብ ተወካዮች ፖርላማ አፈ ጉባኤ የሆኑት አቶ አባዱላ ገመዳ ስልጣናቸውን መልቀቃቸው ይታወሳል።
በአገዛዙ ውስጥ  ፈላጭ ቆራጭ ከሆኑት ግለሰብ መካከል አንዱ እንደሆኑ የሚነገርላቸው አቶ በረከት ስሞኦን በሃላፊነት ከሚያገለግሉበት ሁለት ቁልፍ የመንግስት ስልጣን ለመልቀቅ ጥያቄ ማቅረባቸው ይታወቃል።

የአቶ በረከት ስሞኦን ከስልጣን መልቀቅ እንዳላስገረማቸው እንዲሁም አቶ በረከትን በስራ አጋጣሚዎች እስከሚያውቋቸው ድረስ ጨካኝ እና እምነት የማይጣልባቸው ግለሰብ እንደሆኑ ወ/ሮ አና ጎሜዝ ገልጸዋል።
በኢትዮጵያውያን ላይ ለፈጸሙት ወንጀል ለፍርድ መቅረብ ይኖርባቸዋል በማለት ፖርቹጋላዊዋ  ወ/ሮ አና ጎሜዝ በአቶ በረከት ስሞኦን ዙሪያ ተጨማሪ አስተያየታቸውን አስፍረዋል።

አቶ በረከት ስሞኦን እንዲህ በቀላሉ ስልጣናቸውን ለመልቀቅ የደረሱበትን ውሳኔ ሌላኛው አገዛዙን በስልጣን የማቆያ ስልት ሊሆን ይችላል የሚል አስተያየቶች እየተበራከቱ ይገኛሉ።
በተለያዩ የኦሮሚያ ክልሎች በርካታ ንጹሃን ሰዎች ሲገደሉ፣ ገሚሱ ሲታሰሩ፣ የቀሩት ደግሞ ሲሰደዱ ተቃውሞ ያላሰሙት አቶ አባዱላ ገመዳ ከስልጣናቸው መልቀቅን ተከትሎ የህውሃትና የብአዴን የደም ስር የሆኑት አቶ በረከት ስምኦን ተመሳሳይ የስራ መልቀቂያ ማስገባት አገዛዙ ከወትሮ ለየት ያለ ስልትን ይዞ ቀርቧል የሚሉ ትንታኔዎች በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያዎች ይሰነዘራሉ።